# ዓለምለኸ ማሕበር ዴሞክራሲያዊያን ተጋሩ

## አለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር.

## International Tigrean Democratic Association

itda2005@yahoo.com


### ሉአላዊነትን የማያስከብር የመጀመሪያው መንግስት

በአሁኑ ጊዜ አሳሳቢ ከሆኑት የኢትዮጵያ ህዝብ ችግሮች አንዱ በኢትዮጵያ መንግስት ለሱዳን መሬት መስጠቱን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ችግር ካገር ውስጥ፣ ማለትም ከመንግስት የሚመጣ በመሆኑ በታሪካችን አዲስ ነው፤ ከኢሕአዴግ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ግን የማይጠበቅና በድንገት የወረደብን ዱብ ዕዳ አይደለም፡፡

ያለን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ከሕዝብ ተደብቆ ክህደት ሲፈፅምና ሲዋሽ ማጋለጥ ይቻላል፤ ክህደቱን የሚፈፅመው በዋናነት በጉልበት ስለሆነ ግን በሰላማዊ መንገድ ጥፋቶቹን ማረም አይቻልም፡፡ ይህ ህዝብን አሸማቅቆ የያዘው አገዛዝ በሚፈፅማቸው ወንጀሎች እሱም ራሱ የህዝብ ቁጣን እየፈራ ስለሚኖር ከስልጣን እስኪወገድ ድረስ የሽብር ድርጊቶቹን አያቆምም፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በውጭ ወራሪዎች ሉአላዊ መሬቱ ሲደፈር በህብረት ተነስቶ በመመከትና ነፃነቱን በመጠበቅ በተለይ ለጥቁር ህዝቦች አርአያነት ያለው ታሪክ አለው፡፡ ይሁን እንጂ መለስ ዜናዊ የሽብር አገዛዝ መስርቶ የኢትዮጵያን መሬት እንደ ገፀ በረከት ለባእድ እያደለ ነው፡፡ ስለዚህ የአገራችን የዳር ድንበር ችግር ከመለስና ግብረ አበሮቹ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ለሱዳን የተሰጠው የመሬት ሁኔታ ከአገዛዙ ዓላማና ድርጊቶች ጋር አያይዘን ጥያቄዎች እያነሳንና የታሪክ መሠረት ይዘን መመርመር ያስፈልገናል፤ ምክንያቱም መለስ ካልተገታ በኢትዮጵያ ህልውና ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

### 1. እውነቱ ምንድን ነው? መለስ ለሱዳን መሬት ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም?

ለምና ሰፊ የአገራችን መሬት ለሱዳን እንደተሰጠ በኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በተደጋጋሚ መግለጫዎች ወጥቷል፤ ጉዳዩ የችግሩ ሰለባ በሆኑ ወገኖቻችንም በአሜሪካና ጀርመን ሬድዮች ተብራርቷል፡፡ የኢህአዴግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግን በኢትዮጵያውያን የሚገለፀውን ጭንቀትና ተቃውሞ "እጅግ አስፀያፊ የሆነ አሉባልታ" ብሎ ማጥላላቱ የሚታወስ ነው፡፡

ማን እውነት እንደሚናገር ለማጣራት ብዙ ጊዜ ሳይፈጅ የሱዳን ጋዜጦችና ባዲስ አበባ የሚገኙ የሱዳን ዲፕሎማት ሱዳን ከኢትዮጵያ መሬት ማግኘቷን አረጋግጧል፡፡ የሱዳን ጋዜጦችና ዲፕሎማቶች ምስጢሩን አለመጠበቃቸው በመለስ የተሰጣቸው መሬት በምስጢር መሆኑ ተነግሯቸው ስላልቆየ ሊሆን ይችላል፡፡ የመለስ ተላላኪው ስዩም መስፍን ተቻኩሎ ወደ ሱዳን የሄደበት ምክንያትም ምስጢሩን ለመደበቅ ያደረገው ሙከራ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም የፈለገው ቢያወራ ምስጢሩን መደበቅ አልተቻለም፡፡

## 2. አገዛዙ ለምን እውነቱን ለመደበቅ ሞከረ? ለምን ተቆጣ? ለምን አስፈራራ?

ታድያ አስፀያፊው ድርጊት የፈፀመው ማን ነው? የመለስ አገዛዝ የኢትዮጵያ ህዝብ ሳያውቀው መሬት ሰጥቶ ሲያበቃ ድርጊቱን በምስጢር የሚይዝበት ምክንያት ምንድን ነው? ምስጢሩ ሲጋለጥ ለምን ካደ? ያጋለጡበትን ወገኖች "እጅግ አስፀያፊ የሆነ አሉባልታ" እንዳሰራጩ ወንጅሎ፣ ለምን እነዚህን ወገኖች አሰፈራርቶ አፋቸው ለማስዘጋት ሞከረ?

የመሬት ስጦታው የችግሩ ሰለባ የሆኑት እየገለፁትና የሱዳን መንግስት እያመነበት ኢህአዴግ ጉዳዩ ያለቀና ያበቃለት እኪሆን ድረስ (in order to create facts on the ground) ጊዜ ካላሰፈለገው በስተቀር ለምን በምስጢር ያዘው? ኢህአዴግ መሬት እንዳልሰጠ እየገለፀ ቆይቶ ምስጢሩን መደበቅ በማይችልበት ደረጃ ላይ ሲደርስ "ሱዳን የወሰደችው የራስዋ እንጂ የኢትዮጵያ እንዳልነበረ" በማመካኘት እንደሚያጭበረብር የታወቀ ነበር፡፡ ይህም አደረገ፡፡

መለስ በ21.05.2008ዓ/ም እ.ኤ.አ በተናገረው መሠረት በ1996ዓ/ም በኢትዮጵያውያን ተይዞ የነበረ የሱዳናውያን ኢንቨስተሮች መሬት ለሱዳን እንደተሰጠ አድበስብሶ አምኗል፡፡ ባገራችን ተጠያቂነት ቢኖር ኖሮ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ ቃል አቀባዩና ባለደረቦቻቸው ከስልጣን መወገድ ነበረባቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሌሎቹ ሲዋሹበት የሰነበቱበት ጉዳይ መለስ ሳይፈልገውና ሳያውቀው ሊሆን አይችልም፡፡ ሌሎቹ ባለስልጣኖችና ካድሬዎች መለስ ያልፈቀደላቸው መግለጽ ስለሚፈሩ መሬት መሰጠቱን እየካዱ ብቻ ሳይሆን መሬት እንደተሰጠ ያጋለጡትን ወገኞች እየሰደቡ፣ እያወገዙና እያጥላሉ ሰነበቱ፡፡ ተሳዳቢዎቹ ቅን ሕሊና ቢኖራቸው ማፈር (ግለ ሂስ ማድረግ) ቢገባቸውም አያደርጉትም፤ ምክንያቱም ወንጀል መፈፀም፣ ወንጀሉን በምስጢር መያዝ፣ ወንጀሉ ሲጋለጥ አሌ ማለትና ወንጀሉን ያጋለጡትን ማጥላላት፣ ወንጀሉን መካድ ሲያቅታቸው ደግሞ ሌላ ውሸትና ምክንያት መፍጠር በመለስ ጠባይ የተገነባ ያገዛዙ አሠራር ነው፡፡ ይህ አሰራር መለስ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ይቀጥላል፡፡

## 3. ለሱዳን የተሰጠው መሬት ተገቢነት አለው ወይስ የለውም?

አሁንም መለስ መሬት ለሱዳን መስጠቱን ስላመነ የስጦታው ተገቢነትና ለዛ የሰጠው ምክንያት ማመን አንችልም፡፡

የኢህአዴግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እ.ኤ.አ. በ1972 ከሱዳን ጋር "ተደረገ' የሚለውን ስምምነት ተግባራዊ ለማድርግ በ2001 ባቋቋመው ኮሚቴ እንደሚሰራ አምኗል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን እንደፃፉት ግን ያ ስምምነት የንጉሰ ነገስቱ ምክር ቤት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ከኢህአዴግ የምክር ቤት አባሎች የዛን ያህል ላገር ተቆርቋሪነትና ላገር ሉአላዊነት የመቆም ወኔ መጠበቅ አስቸጋሪ ቢሆንም ያሁኑ ምክር ቤት መሬት ከመሰጠቱ በፊት ጉዳዩን ሊያየው ይገባ ነበር፡፡ ሌላ ነገር ካልተከሰተ ምክር ቤቱ ከመለስ ተግሳፅ አዘል ትምህርት ተቀብሎ ውሳኔውን በኢህአዴግ አባላት በሙሉ ድምፅ ስለሚደገፍ ግን ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ ቢነጋገርም ትርጉም አይኖረውም፡፡

ሆኖም እንደ ፕሮፌሰር መስፍን አባባል በቢሮክራቶች ጥናት ላይ የተመሰረተው የ1972 የውሳኔ ሃሳብ ውድቅ ከመሆኑም በላይ በደርግ ጊዜ በፕሮፌሰር መስፍን የተመራ የዩኒቨርሲቲ ቡድን የተሻለ ጥናት አድርጓል፡፡ ሁለተኛው ቡድን በመጀመሪያው ጥናት ያልተካተቱ መረጃዎች ስለጨመረ ለምና ሰፊ የኢትዮጵያ መሬት በኢትዮጵያዊነቱ እንዲፀና የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ኢህአዴግ ሁለተኛውንና የተሻለውን ትቶ ለምን ኢትዮጵያን የሚጎዳውንና ውድቅ የሆነውን ስምምነት መረጠ? "ለቀባሪው

አረዱት" እንደሚባለው ፕሮፌሰር መስፍን ኢትዮጵያን የሚጠቅም አማራጭ እንዳለ እየገለፁ መለስ ፕሮፌሰር መስፍን የሙሩት ቡድን "**የጎይን መስመር ከመቀበል አማራጭ እንደሌለ**" እንደገለፀ አድርጎ አቅርቦታል፡፡ መለስ እውነት ሲናገር እንደሚታወቀው እንግዲህ በሂግ ፍርድ ቤት በዝረራ ማሸነፋን እንደገለፀው አይነት ነው፡፡ ስለዚህ መለስ የቀረው ነገር ቢኖር ከምርጫ 97 በሁዋላ የተፈፀመውን ጭፍጨፋ ያጣራውን ኮሚቴ ውጤት እንዳስቀየረ፣ እነ ፕሮፌሰር መስፍንም የጥናት ውጤታቸውን ማስቀየር ወይም ደግሞ እነ ፕሮፌሰር መስፍንን በሽማግሌ ይቅርታ እንዲጠይቁ ማስገደድ ነው፡፡ ሪፖርተር በ25.05.2008 "መሬት ሰላምን ያስገኛል? በሚል ርእስ ሥር እንደፃፈው "**በድንበር ጉዳዩ ታሪኩ ላይ ጥናት አድርገዋል የተባሉትንና የታሪክ ምሁሩን አስተያየት እንዲሰጡን ጠይቀን ፈቃደኞች ሊሆኑ አልቻሉም**"፣ የሚለው ሰዎቹ መለስ የማይፈልገው እውነት መናገር ፈርተው ሊሆን ይችላል፡፡

በተጠቀሰው የሪፖርተር ፅሑፍ አቶ አግባው ሰጠኝና አቶ ልብሰወርቅ ጥሩነህ መሬት መሰጠቱን ገልፀዋል፡፡ መለስ የገለፀው ግን ሁለቱ ኢትዮጵያውን ያቀረቡትን የምስክርነት ቃል የሚቃረን ነው፡፡ አቶ አግባው ባካባቢው እንደተወለዱና ኢትዮጵያውያን ያረሱት መሬት ከተወለዱ ጀምረው የኢትዮጵያ መሆኑን እንደሚያወቁ ሲገልፁ፣ መለስ ለሱዳናውያን ኢንቨስተሮች "የተመለሰው" መሬት ከጎይን መስመር በስተምእራብ እንደሆነና ከ1996 እኤአ. ወዲህ በኢትዮጵያውያን እንደተያዘ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ፕሮፌሰር መስፍን ከጋላባት ካንድ ነጥብ ተነስተው ከደቡብ ምእራብ ወደ ሰሜን ምስራቅ እየሰፉ የሚሄዱ ሁለት መስመሮች እንዳሉ ሲጠቅሱ፣ መለስ የሚያወራው ስለ አንድ መስመር ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሱዳን ወታደሮች በመለስ ፈቃድ የኢትዮጵያ ሉአላዊ መሬት በጋምቤላ በኩል እንደተቆጣጠሩና ሕዝብ እንዳፈናቀሉ ታፍኖ የቆየው ሃቅ አሁን ጋሃድ ሆኗል፡፡ እነዚህ በሱዳን ወታደሮች የሚንገላቱት ኢትዮጵያውያን የሚያምኑት በአገራቸው ውስጥ እንደሚኖሩ ነው፡፡ መለስ የነዚህ ዘጎች እምነት ባይጋራም በባእድ ወታደሮች እንዲጠቁ መፍቀዱ ከኢትዮጵያዊም ከማንም መንግስትም የማይጠበቅ አስነዋሪ ድርጊት ነው፡፡ የተጎጂዎቹ ዜጎች ሰሞች በዝርዝር ተገልፆ እያለና ድምፃቸው በሬድዮ እየተሰማ፣ መለስ ደጋግሞ አንድ ኢትዮጵያዊ እንዳልተፈናቀለ ሲናገር ከክህደት ውጭ ምን ሊባል ይችላል?

ከኢህአዴግ በፊት መንግስት መሬት ለሌሎች አገሮች በድብቅ ይሰጣል የሚል ስጋት የኢትዮጵያ ህዝብ ኖሮት አያውቅም፡፡ ይህ አይነት ስጋት በንጉሱና በደርግ ዘመን ያጋጠመበት ጊዜ አልነበረም፡፡
አሁን ግን አዲስና ከነበሩት ችግሮች የባሰ አደገኛ ችግር ተፈጥሯል፡፡ ኢህአዴግ የሚያራምደው ፖለቲካ አገር በመሸራረፍ፣ የባህር በር አሳጥቶ የፀጥታ አደጋና የኢኮኖሚ ማነቆ በማመቻቸት፣ ህዝብን በቋንቋ ከፋፍሎ አንድነት በማላላት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች የገዢዎቻችን የስልጣን እድሜ ከማራዘም አልፈው የኢትዮጵያ እንደ አገር መኖርን ሊፈታተኑ ይችላሉ፡፡ ህዝባችን ባገዛዙ ጭፍጨፋዎች ስለተሸማቀቀ ያገዛዙ ጉጂ ድርግቶች ለጊዜውም ቢሆን ማረም አልቻለም፡፡ አገዛዙ ኢትዮጵያውያንን እየገደለና እያሰቃየ ከመግዛት በላይ ኢትዮጵያን እንደ አገር እየከፋፈለና እየቆራረጠ ሊያፈራርሳት ይችላል፡፡ ይህም ካለ ምክንያት የመጣ ወይም አገዛዙ እንደሚለው "የፖለቲካ አጀንዳ ለማራመድ" የሚደረግ ቅስቀሳ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ ለወደፊቱ አያደርገውም ባይባልም እሰካሁን ድረስ ስላላደረገው ተቃወሚዎች ለኬንያ ወይም ለጅቡቲ መሬት እንደተሰጠ ሲገልፁ ተደምጠው አያውቁም፡፡

## 4. የመለስ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ መስጠት ተዳጋጋሚነት

በ1969 ዓ/ም የዚያድ ባሬ ሰራዊት እስከ 700 ኪሎ ሜትር ያህል ዘልቆ ሰፊ የኢትዮጵያ ሉአላዊ መሬት ተቆጣጥሮ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሃገሩን ሉአላዊነትና ዳር

ድንበሩን ለማስከበር ከደርግ ጋር ተባብሮ ወራሪውን ሠራዊት አስወጣ፤ ወረራው ተቀለበሰ፤ ደርግም በተቆጣጠረው የኢትዮጵያ መሬት ድርድር አላደረገም፣ በዚያ በኩል ሰላም ሰፈነ፡፡

በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል በተከሰተው ግጭት ግን መለስ በጦርነት የተገኘውን ድል ወደ ሽንፈት ቀይሮታል፤ መሬት ሰጥቷል፤ ሉአላዊነትን ከመሬት ለመለየት ሞክሯል፤ መስዋዕት ከፍለው ነፃነት ያቆዩልን ትውልዶች ድህነት እንዳቆዩልን ሊያስተምር ሞክሯል፡፡ ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት የዓለም የመጨረሻ ድሃ አገሮች ተወካይ የሆኑት ሚስተር ቻይክ ሲዲ ዲያራ በአዲስ አበባ በተደረገ ስብሰባ ላይ ስለ ወደብ አልባ አገሮች ባደረጉት ንግግር፤ ወደብ አልባ የሆኑ ታዳጊ አገሮች ለእድገት የሚያስፈልግ እርዳታ ቢጨመርላቸው፣ ዕዳ ቢሰረዝላቸውም ሆነ በዓለም ገበያ ለመሳተፍ ሁኔታ ቢመቻችላቸው በዓለም ኢኮኖሚ ያላቸው ድርሻ የዳር ተመልካችነት ሆኖ እንደቀረና መሠረታዊ ለውጥ እንዳላስመዘገበ ገልጿል፡፡ ቀጥለውም በተለይ ወደብ አልባ የሆኑ የአፍሪካ አገሮች በከፋ ሁኔታ እንደሚገኙ አስምረውበታል፡፡ (አባይ ሚድያ ኒውስ፣ ሰኔ 11፣ 2000 ዓ/ም) መለስ ግን የባሕር ወደብ ቱሪስቶች እንደሚያርፉበት ሆቴል እንደሆነ በማጭበርበር 80 ሚልዮን ኢትዮጵያውያንን ለማሞኘት ሲሞክር ምን ያህል ቅንነት እንደሌለው በግልፅ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የችግሩ አዲስነት ኢሕአዴግ የሚያስገድደው ሁኔታ ሳይፈጠር መሬታችንን በፍልጐቱ ይሰጥብናል ከሚል ስጋት የመነጨ ነው፡፡ ይህ የስጋታችን ምንጭ የሆነው በመንግስት ደረጃ የሚፈፀም ክህደት በኢትዮጵያም በዓለምም አጋጥሞ የማያውቅ ልዩ የክህደት ክስተት ነው፡፡

## 5. መለስ ከመጀመሪያ ጀምሮ ኢትዮጵያን የሚጠቅም ራእይ አልነበረውም

ይህ አገዛዝ በተቃዋሚዎች የፈጠራ ወሬ ሳይሆን በተጨባጭ በራሱ ባገዛዙ ዓላማና ድርጊቶች ምክንያት አገሪቷን ይጐዳታል የሚል ከፍተኛ ስጋት አለ፡፡ ይህ ስጋት የተሓህት አመራር በ1968 በይፋ ካወጣው ትግራይን የመገንጠል ዓላማ ጀምሮ የተከሰተ ነው፤ ከዛም በሁዋላ ስጋቱን የሚያጠናክሩ አቋሞች ተወስደዋል፤ ድርጊቶች ተፈፅሟል፡፡

መለስ ከግብረ አበሮቹ ጋር በ1968 የህወሓት (በዛን ጊዜ ተሓህት) አላማ የትግራይ ሪፑብሊክ መመስረት እንደሆነ በማኒፌስቶ ስም ያረቀቀው ሃሳብ (በስዩም መስፍን እጅ ተፅፎ፣ ወደ ሱዳን ተወስዶና ታትሞ የተሰራጨው) በኖ የጠፋ ሃሳብ አይመስልም፡፡ ሃሳቡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ባለማሰብ፣ በጥላቻና በስልጣን ጥም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ **ኢትዮጵያውያን ለመጀመሪያ ጊዜ ከውስጥ የሉአላዊነት ችግር ሲያጋጥመን ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያዊነትን የሚቃወም ዓላማ ይዘው የተነሱ ሰዎች ስለሚገዙን መሆኑ ማንም ሰው ከተሓህት ማኒፌስቶ መገንዘብ ይችላል፡፡**

ያገዛዙ ጐጂ ድርጊቶችም የመለስ ፀረ-ኢትዮጵያ ራእይ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴረሽን ከመተሳሰሯ በፊት በነበሩ ድርድሮች የጣልያን ተወካይ (ስፎርሳ) ሳይቀር አሰብ የኢትዮጵያ የባህር በር እንድትሆን ይደግፍ ነበር፡፡ አቶ ታምራት ላይኔ ለፍርድ ቤት ባቀረቡት ፅሁፍ እንደገለፁት፣ መለስ በሎንዶኑ ድርድር ጊዜ ይሁን በአህአዴግ አመራር ውስጥ የወደብ ጉዳይ እንዲነሳም አልፈለገም፡፡ ከዛም በላይ ኤርትራ ኢትዮጵያን ስታጠቃ የመከላከል ዝግጅት እንዳልነበረ፤ የአልጀርሱ ጉዞ ለኢትዮጵያ ጉዳት እንጂ አስፈላጊነትም ጥቅምም እንዳልነበረው፤ የሄጉ ክርክር ፍሬ ቢስ እንደሆነና በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መስዋእትነት ከከፈሉ በሁዋላ ስለ ባድመ በየጊዜው ምን እንደተባለ የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቀዋል፡፡ የኤርትራ መንግስት ቡሬ ላይ ለጥቂት አመታት (ከ1994 እስከ የ1998 እኤአ የመጀመሪያ ወሮች) መስሪያ ቤት ስለነበረው ቡሬን የኤርትራ ሉአላዊ ግዛት እንደነበረች በማቅረብ ቦታውን መጋራት ሲችል፤ መለስ ሁል ጊዜ ከኤርትራ ውጭ በኢትዮጵያ ስትተዳደር የነበረችውን ባድመ

የኢትዮጵያ መሆንዋን የሚያረጋግጡ በቂ ማስረጃዎች አላቀረበም፡፡ ፈራጆቹ ያሮና እና ፎርት ካርዶና በውሉ መሰረት የኢትዮጵያ መሆናቸውን ለማስረዳት ማስረጃ ሲያቀርቡ መለስ በፅሑፍ ተቃውሞ አቅርቧል፡፡ ስለዚህ ያለን "መንግስት" ሉአላዊነትንና፣ ዳር ድንበርን የማያስከብርና የህዝብ ጥቅምን የማያስጠብቅ ነው፡፡

## 6. ጕሰኝነትና ዘረኝነት

በኢህአዴግ ውስጥ ህወሓት ወሳኝነት አለው፤ የህወሓት ወሳኝነት ግን በጉልበት መሳሪያነት ብቻ ነው፡፡ ከፍተኛ ያገር ጉዳዮች የሚወሰኑት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲሆን አብዛኞቹ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፅ/ቤት በሚኒሰትርነት ደረጃ ያሉ ከፍተኛ አማካሪዎች የሚያገናኛቸው የህወሓት አባልነት ሳይሆን ጕሰኝነት ነው፡፡ ያ ፅ/ቤት ሁሉንም የሚያሽከረክር በመንግስት ውስጥ የበላይ መንግስት ሆኖ ለራሱ በስልጣን ከሚያገኘው ጥቅም በላይ የኢትዮጵያን ደህንነት አያስቀድምም፡፡

የመለስ አገዛዝ ህዝብን እያጣላ በመከፋፈል የታቃዋሚዎች ትግልን ለማዳከም በካድሬዎቹ ጎሰኝነትን እያጠናከረ ወደ ዘረኝነት ተሸጋግሯል፡፡ የመለስ ደጋፊዎች መሬት ለሱዳን መሰጠቱን ያጋለጡት ኢትዮጵያውያንን በዘረ-ቢስነት ፈርጀዋል፡፡ ለመሆኑ ከናዚዎች ጭንቅላት ውጭ "ዘረ ቢሶች" የሆኑ ህዝቦች በዓለም ውስጥ አሉ? በሂትለር መፅሀፍ (ማይን ካምፕፍ/ የኔ ትግል) ለሽክም የተመደቡ ህዝቦች ነበሩ፤ሌሎችም ሌሎችም፡፡ የተለያዩ ዘሮች በእኩልነት በሚተያዩበት በሰለጠነ የ21ኛ ክፍለ ዘመን በዘር የማይለያይ ህዝብ በሚኖርባት አገራችን ዘረኝነት ሲሰበክ ግን ያሳፍራል፤ ዘረኝነቱ ጉዳት ስለሚስከትል ያሳዝናል አጥብቀንም እንቃወመዋለን፡፡ ግልፅነትን የሚፈልጉትና ዳር ድንበራቸውን ለማስከበር የሚታገሉት ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያዊነታቸው ከካሃዲዎች ይልቅ የእነ አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሃንስ፣ አፄ ምኒሊክ ወዘተ. አኩሪ ወገኖች እንደሆኑ ግን ላንድ አፍታም አንጠራጠርም፡፡

የሚያሳስበን ግን በመለስና በተከታዮቹ ካድሬዎች የሚሰራጨው ዘረኝነት አይደለም፤ ከነሱ የሚጠበቅ ነውና፡፡ የሚያሳስበን በመለስና ግብረ አበሮቹ ፀረ ኢትዮጵያነት ምክንያት የትግራይ ህዝብን እንደ ጠላት የሚመለከቱ ፅነፈኞችም መኖራቸው ነው፡፡ አገዛዙ ህዝብንና አገርን የሚጐዱ እርምጃዎች በወሰደ ቁጥር፣ ለምሳሌ ባሁኑ ጊዜ መሬት ለሱዳን መሰጠቱን በሚመለከት የትግራይ ህዝብን ካገዛዙ ጋር በጅምላ የሚያጥላሉ ፅንፈኞች ቅስቀሳ ያካሂዳሉ፡፡ የትግራይ ህዝብን በጥቅል ከሚጠሉት መሃከል ለጊዜው በስሜታዊ ቅስቀሳ ቢሳሳቱም ሊታረሙ የሚችሉ አሉ፡፡ እያወቁ በህዝብ መኸል ጥላቻ በማስፋን ህዝብን የሚለያዩ ድርጅቶችና ግለ ሰቦች ግን የሚወናበዱ ተከታዮች እስካገኙ ድረስ በያዙት ሊቀጥሉ ስለሚችሉ ከማንም ጊዜ በላይ አንድነት የሚያስፈልገውን ትግል እንዳያዳክሙ መወገዝ ይገባቸዋል፡፡

በመስረቱ ሰላማዊ ህዝብ ነፃነት ከሌለውና ካልተደራጀ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ከሚረግጥ የታጠቀ ቡድን ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ራሱን ለመከላከል ዝግጁ አይደለም፡፡ ስታሊን፣ ሂትለር፣ ሙሶሊኒ፣ ፖልፖት፣ ኢዲ አሚን፣ ታሊባን፣ መንግስቱ ወዘተ. በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ህዝቦችን አንደተቆጣጠሩ ሁሉ መለስም የትግራይ ህዝብን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብን በጠቅላላ እየተቆጣጠረ ነው፡፡ በመለስ ስርአት ላይ ሁሉም ጭቁኖች በህብረት እንዲነሱ በማቀራረብ ፈንታ ህዝቡን መለያየት መለስ ወደሚፈልገው ወጥመድ መግባትና የጭቆናውን ጊዜ ማራዘም ይሆናል፡፡

በማጠቃለል ኢትዮጵያውያን ባለው አገዛዝ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን ተነፍገናል፤ ፍትህ አላገኘንም፤ የህግ የበላይነት አልተከበረልንም፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት ችግሮች ካለው አገዛዝ በፊትም በተለያዩ ደረጃዎች የቆዩ ናቸው፡፡ ችግሮቹ ግን

በኢትዮጵያ ላልተለመደ አዲስ የሉአላዊነት ችግር አጋልጠውናል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በዴሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊና ህጋዊ አግባብ መንግስትን መምረጥና ማስወገድ ቢችል ኖሮ ባገራችን የሉአላዊነት አደጋ የሚፈጥሩብን ከሃዲዎች አይገዙንም ነበር፡፡

## 7. ምን እናድርግ?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለብዙ ዘመናት በመንግስታዊ መዋቅር ሲተዳደር የኖረ በመሆኑ በሕብረት ነፃነቱን ከውጭ ወራሪዎች ለመከላከል ችሏል፡፡ ሆኖም ሕዝብ ለመንግስት ያለው ታዛዥነት ነፃ ሆነው የተደራጁና ያልተደራጁ የተለያዩ የሕብረተ ሰብ ክፍሎች በተስማሙበት ሕገ መንግስት መሰረት አይደለም፡፡ ስለዚህ ሕብረተ ሰባችን የየራሳቸው ሕጎች ከሚያወጡና ከሚቀያይሩ ፈላጭ ቆራጭ ግለ ሰቦች መዳፍ አልተላቀቀም፡፡

በ66ቱ አብዮት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደቆየው ባልመረጠውና በሰላማዊ መንገድ ከስልጣን ሊያስወግደው በማይችለው መንግስት መገዛት እንደማይፈልግ በአመፅ አሳይቷል፡፡ ሕዝብ ሳይደራጅ ስለቆየ ደርግ ተደራጅቶና ታጥቆ የቆየውን መለዮ ለባሽ ተጠቅሞ ስልጣን ቢይዝም ሕዝብ ያነሳቸው የዴሞክራሲ ጥያቄዎች በገዢዎች ላይ ፍርሃት ለቋል፡፡ ገዢዎች ስለሚፈሩም የሚፈሩት እንዳይደርስባቸው ማንንም ተቃውሞ በእንጭጩ ለመቅጨት፣ በደርግና በኢህአዴግ እንዳየነው፣ በማሸበር የሚገዙ ስርአቶች ተከስተዋል፡፡ ደርግና ኢህአዴግ አረሜናዊ የሆኑ፣ ሕዝብን ስለሚፈሩ ሕዝብን በጭፍጨፋ አሸብረው የሚገዙ ተከታታይ የሽብር አገዛዞች (successive reigns of Terror) ናቸው፡፡

ኦይገን ኮጐን ስለ ናዚ አገዛዝ በፃፈው መፅሐፍ እንደሚከተለው ይላል፡ "ስልጣን የያዘና ከስልጣን ያልተወገደ አምባገነንነት፣ ገዢ ለመሆን የተጠቀመባቸውን መሳሪያዎች አይተውም፡፡" ከህወሓት ፀረ ዴሞክራሲያዊ አመራር የበቀለው የመለስ አገዛዝም፣ ትልቅ ክብር የሚገባቸው በህወሓት/ኢህአዴግ ለህዝብ መብትና ነፃነት የተሰዉትን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ታጋዮችን ነፃነትና መብት በመከልከል፣ ህዝቡንም በማፈንና በማሸበር ወደ ስልጣን የመጣ አምባገነናዊ አገዛዝ ነው፡፡ ስለሆነም ከስልጣን እስኪወገድ ድረስ ጭፍጨፋን እና አፈናን በበለጠ እያጠናከረ የሚሄድ አምባገነናዊ አገዛዝ ነው፡፡

አስቀድመን እንደገለፅነው የመለስ አገዛዝ ባገራችን ከነበሩት ፀረ ዴሞክራሲያዊ አገዛዞችና እንዲሁም ከሌሎች አገሮች አምባገነናዊ አገዛዞች የሚለየው ግን ምንም ዓይነት አገራዊ ስሜት የሌለው ያገርን መሬት ቆርሶ የሚሸጥ ከሃዲ አገዛዝ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ ስለሆነም መለስና ግብረ አበሮቹ ከስልጣን እንዲወገዱ አለመታገል የኢትዮጵያን አለመኖር ከመቀበል አይለይም፡፡ ስለዚህ የመለስ አገዛዝን ከስልጣን ማስወገድ ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን ነው፡፡ ይህ በማንኛውም የተቻለ መንገድ ይህንን አረመኔያዊ ከሃዲ አገዛዝ ከስልጣን የማስወገድ ግንዛቤና ጥሪ የኢትዮጵያ መኖርን የሚፈልጉ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ እንደ አስቸኳይ ዓላማ ከተቀበሉት ወደ ተግባር ሊተረጐም ይችላል፡፡

ሁሉም በአገር አንድነትና አገዛዙን በማስወገድ አስፈላጊነት የሚስማሙ ሃይሎች አቅማቸውን በእርስ በርስ ሽኩቻ ማባከን አቁመውና በሌሎች ልዩነቶቻቸው ተቻችለው ለኢትዮጵያ ህዝብ አርአያ የሚሆን የዓላማ አንድነት እንዲፈጥሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

መለስ ከስልጣን ይወገድ!!!
የኢትዮጵያ ህዝብ ካንዣበበት አደጋ በአንድነት በአሸናፊነት ይወጣል!!!